## የኢፌድሪ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት
## ስቶክሆልም-ስዊድን

### የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ አጭር ማብራሪያ ሰነድ

ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለመገንባት በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ አገራዊ ስሜትና ቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ:: የህዳሴ ግድቡ አገራችን ድህነትን ለማሸነፍ በሚታደርገው ጥረት ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል:: በመሆኑም በዚህ ታሪካዊ ወቅት የአገራችን ህዝቦች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አካል ለመሆን ቦንድ በመግዛትም ሆነ ስጦታ በማበርከት እንዲሳተፉ ለማስቻል ስለቦንድ ምንነት መሠራታዊ መረጃ እንዲሰጥ ይህ አጭር ሰነድ ተዘጋጅቷል::

**የህዳሴ ግድብ (የአባይ ግድብ)**

- በአገራችን በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ የሚገነባ ትልቅ የሀይል ማመንጫ ግድብ ነው::
- በህዝባችንና መንግስት አቅም ብቻ የሚገነበና ከ80 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ የሚሸፍን ግድብ ነው::
- ከአፍሪካ ትልቁና በአለም ካሉት ትላልቅ ግድቦች አንዱ የሆነና ከ6000 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ሀይል የሚያመነጭ ግድብ ነው::
- አገራችን በGTP ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ለኢንዱስትሪ መሪ ኢኮኖሚ የሚታደርገውን ትግል ይደግፋል
- ከፍተኛ የስራ ዕድል የሚፈጥርና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድበት ግድብ ነው::
- ሀገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገውን ጉዞ የሚያፋጥን ግድብ ነው::
- በየጊዜው ወንዙ በሚወስደው ደለልና ጎርፍ ለሚጠቁት ግብፅና ሱዳን ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ግድብ ነው::
- በትነት መልክ የሚባክነውን ውሃ መጠን በእጅጉ በመቀነስ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚደረግ ግድብ ነው::
- ሱዳን በየአመቱ ለመስኖ ግድቦቿ ከጭቃ ለማፅዳት ታወጣው የነበረው 12 ሚሊየን ዶላር ታድናለች::
- ጎረቤት አገሮችና ሌሎችም በአነስተኛ ዋጋ የኤሌክትሪክ ሀይል ያገኛሉ::

## የህዳሴው ግድብ ቦንድ ባህሪያት

**1. ቦንድ ምንድን ነው?**

- ቦንድ መንግሥት ሙሉ ዋስትና የሚሰጠው ወለድ የሚገኝበት ተመልሶ የሚከፈል የብድር ሰነድ ነው::
- የህዳሴው ግድብ ቦንድ የኢትዮጵያ መንግስት በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባውን ታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ለመገንባት የሚያስችል ፋይናንስ ማሰባሰብ እንዲቻል ለሽያጭ የቀረበ ቦንድ ነው::

**2. የቦንዱ ዓይነት፣**

- ወለድ የሚከፈልበት ኩፖን ቦንድ
- ወለድ የማይከፈልበት ኩፖን ቦንድ

**3. ቦንድ የሚሸጠው፣**

- ለኢትዮጵያዊ ወይም ትውልዱ ኢትዮጵያዊ
- ለጎረቤት አገሮችና ለአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጎች

**4. ቦንዱ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች**

- ከቦንዱ ግዢ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው::
- ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንኮች ብድር መውሰድ ይቻላል::
- ለገዢው/ለደንበኛው/ ቋሚ የወለድ ገቢ ያስገኛል::
- የመንግስት ዋስትና ስላለው ከስጋት ነፃ ነው::
- ከመደበኛ ባንክ የቁጠባ ወለድ የተሻለ የወለድ ገቢ ያስገኛል::
- ለደንበኛው/ለገዢው/ ህጋዊ ወራሾች ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ ይችላል፡

**5. የቦንድ ዋጋ**

- ዝቅተኛው የቦንድ ዋጋ (minimum bond value) በዶላር፣በዩሮ በፓውንድ ስተርሊንግ 50 ሆኖ ባለ 100፣300፣500፣1,000፣3,000፣5,000 እና 10,000 ቦንዶችም ለገበያ ቀርበዋል::
- የቦንዱ ሽያጭ የሚከናወነው በዶላር፣ፓውንድ ስተርሊንግ፣ዩሮ፣ስዊዝ ፍራንክ፣ሪያል፣ድርሃም፣ስዊድሽ በዴንማርክና ኖርዌይ ክሮነር እንዲሁም

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚገበያይባቸው ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ይሆናል::

- ከ500 ዶላር በላይ በራሱ ወጪ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ላደረገ ሰው የመላኪያ ገንዘቡ መንግስት ይችላል::

**6. ቦንዱን ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች፣**

- በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ፓስፖርት ወይም የኮሙኒቲ መታወቂያ፤
- በውጭ ሀገር የሚኖሩ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ዜግነት የወሰዱበት ሀ□ር ፓስፖርት እና የኢትዮጵያዊነት ማረ□□ መታወቂያ ወይም የኮሙዩኒቲ መታወቂያ፣
- የጐረቤት አገሮችና የአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጐች ትውልዳቸውን የሚያሳይ ፓስፖርት ወይም ሌላ ህጋዊ ዶክመንት፤
- አንድ ጉርድ ፎቶግራፍ (passport size) ማቅረብ/በቆንስላ ፅ/ቤታችን e-mail አድራሻ መላክ ይችላሉ::

**7. የቦንዱ የክፍያ ጊዜና ወለድ**

*7.1. የሚከፈለው የወለድ መጣኔ የቦንዱን የክፍያ ጊዜ ያገናዘበ ሆኖ*

- *5 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው ------LIBOR+1.25 በመቶ*
- *ከ6--7 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው ------LIBOR+1.5 በመቶ*
- *ከ8--10 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላላቸው ------ LIBOR+2.0 በመቶ ይሆናል::*

*7.2. ወለድ በየስድስት ወሩ ይከፈላል*

- *ወለዱን አገር ቤት ባለ ሂሳብዎ እንዲገባ ማዘዝ ይችላሉ*
- *ወለዱን የሚቀበል ወኪል ማድረግ ይችላሉ*
- *በወለዱ ተጨማሪ ቦንድ እንዲገዛ ማዘዝ ይችላሉ*
- *ወለዱ ባሉበት አገር እንዲመጣ መላኪያውን ችለው ማዘዝ ይችላሉ*

*7.3. ከክፍያ ጊዜ በፊት ስለሚመለሱ ቦንዶች*

*ገዥዎች ቦንዱን ከክፍያ ጊዜ በፊት መመለስ ይችላሉ፣ በዚሁ መሰረት*

- *ከ1-5 ዓመት የሆነ ቦንድ የገዙት ቦንዱን ከገዙበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 1 ዓመት ጠብቀው ገንዘቡን መውሰድ ይችላሉ::*
- *ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ቦንድ የገዙት ቦንዱን ከገዙበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 3 ዓመት ጠብቀው ገንዘቡን መውሰድ ይችላሉ::*

**8. የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ወገን ስለማስተላለፍ**

- ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚችለው በውጭ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ፣ ለትውልድ ኢትዮጵያዊ ወይም የቦንዱን የመግዛት መብት ላላቸው የጐረቤት ወይም የአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጎች ለሆኑ ነው:: ነገር ግን ቦንዱ በሀገር ውስጥ ገንዘብ እንዲከፈልለት ከፈለገ በሀገር ውስጥ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ቦንዱን መግዛት ለሚችሉ ዜጐች ማስተላለፍ ይችላል::
- ቦንድ ገዥው ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን በጀርባው ላይ በመፈረም ብቻ በውርስና በስጦታ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤ ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ገንዘብ መበደር ወይንም ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ/Secondary Market/ ለሌላ ገዥ መሸጥ ይችላል::

---

**9. የህዳሴ ቦንድ በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት፣**

- የህዳሴ ቦንድን ለሌላ ሰው መግዛት ይቻላል:: ነገር ግን ቦንዱ ላይ ስሙ የሚፃፈው ቦንዱ የሚገዛለት ሰው ስም /የቦንዱ ባለቤት/ መሆን አለበት:: በሌላ ሰው ስም ቦንዱን የሚገዛው ሰው በቦንዱ ላይ "ስለ" ብሎ መፈረም ይችላል:: በየጊዜው የወለድ ክፍያ የሚፈፀመውና ዋናው ገንዘብ ተመላሽ የሚደረገው ግን ቦንድ ለተገዛለት ሰው ወይም ህጋዊ ውክልና ለተሰጠው/ጣት ብቻ ነው::
- ለአቅመ አዳም/ሔዋን ላልደረሱ ልጆች በወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው አማካኝነት በቦንዱ ላይ የልጁን/ቷን ስም በመፃፍና "ስለ" ብለው በመፈረም ቦንዱን መግዛት ይችላሉ:: ልጅ/ቷ 18 ዓመት እስከሞላው/ት ድረስ ከቦንዱ የሚገኘው ጥቅም እንዲቀመጥ ወላጅ/አሳዳጊ ከፈለገ በዚሁ መሠረት ማስተናገድ ይቻላል::

**10. ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች**

- የክፍያውን ገንዘብ በስዊፍት ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ correspondent bank በኩል የኢትዮጵያ ንግድ

ባንክ የSWIFT ግንኙነት ካላቸው 40 ታላላቅ ባንኮች ጋር (ከዌብሳይታችን ዋናውን ሰነድ ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ) የcorrespondent banking ግንኙነት አለው::

- እነዚህ ባንኮች በብዙ ሀገራት ቅርንጫፎች ያሏቸው በመሆኑ ማንኛውም ቦንድ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ወደ እነዚህ ቅርንጫፎች በመሄድ በቀላሉ ገንዘቡን ማስተላለፍ ይችላል::
- በአገር ቤት የዲያስፖራ ሂሳብ ካለዎት በዛ መግዛት ይቻላል
- በጥሬ ገንዘብም መግዛት ይቻላል

***ካንዴነቪያን አገሮች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ በትብብር ከሚሰሩ ባንኮች ጥቂቶቹ፡-***

| Currency | Name of the Bank | State |
|---|---|---|
| SEK | Nordea Bank AB (pub 1) | Stockholm |
| SEK | SEB/Skandinaviska Enskilda, Banken AB(Pub 1) | Stockholm |
| SEK | Svenska Handlesbannken AB | Stockholm |
| DKK | Danske Bank A/S | copenhagen |
| DKK | Danske Bank A/S | copenhagen |
| CITIEGCX | CALYON (HELSINKI) | HELSINKI |
| ESSEFIHX | SKANDINA VISKA ENSKILDA BANKEN | HELSINKI |
| HANDFIHH | SVENSKA HANDELS BANKEN | HELSINKI |
| NDEAFIHH | NORDEA BANK FINLAND PLC | HELSINKI |
| OKOYFIHH | OSUUSPANKKIEN KES-KUSPANKKI OYI (OKO BANK) | HELSINKI |
| PSPBFIHH | SAMPO BANK PLC (HEAD OFFICE) | HELSINKI |
| CITIEGCX | CALYON (HELSINKI) | HELSINKI |
| DNBANOKK | DNB NORBANK ASA (FORMERLYDENNORSKE BANK ASA) | OSLO |
| ESSENOKX | SKANDINAVISKA ENSKILDA BANKEN | OSLO |
| HANDNOKK | HANDLS BANKEN | OSLO |
| LABANOKK | BANK 1 OSLO AS | OSLO |
| NDEANOKK | NORDEA BANK OF NORGE ASA | OSLO |

***<u>LIBOR:</u>*** *London Interbank Offer Rate ማለትም በለንደን የገንዘብ ገበያ ባንኮች በየዕለቱ እርስ በርሳቸው የሚበዳደሩበት የወለድ መጣኔ ነው:: ይህ መጣኔ ብዙ ባንኮች የራሳቸውን የወለድ መጣኔ ለመወሰን እንደመነሻ የሚጠቀሙበት ነው:: የምጠኔ መጠኑን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድህረ-ገጽ ላይ መመልከት ይችላል::*

**11. ለግድቡ የሚደረጋውን ስጦታ በተመለከተ**

- ለህዳሴ ግድብ ግንባታታ ነፃ የገንዘብ ስጦታታ ማበርከት ይቻላል፣
- ስጦታውን የሚለግሰው ግለሰብ ባቀረበው የገንዘብ መጠን ልክ ህጋዊ ደረሰኝ ይሰጠዋል::

**12. በታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ አገዛዝና ስጦታ ማብራሪያ ቢሹ**

ከዚህ በታች በተመለከተው አድራሻ ይጠይቁ -

*በስቶክሆልም የኢትዮጵያ ቆንስል ጀኔራል*

- *E-mail* ***ethemb.community@telia.com***
  ***<u>ethemb.all@telia.com</u>***
- *Telephone Number*
  *+ 46-8661 61 58*
  *+ 46-8661 63 25*
  *+ 46-8661 63 48*
- *Fax +* ***46-8660 81 77***
- Web-site *<u>http://www.ethemb.se/</u>*

*የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግንኙነት ለማድረግ ስፈልጉ ቀጥሎ ያሉትን አድራሻዎች ይጠቀሙ*

- *E-mail: hidasebond@combanketh.com*
- *P.O.Box* ***በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ***
  ***ፖ.ሣ.ቁ 255***
  ***አዲስ አበባ***
- *Web-site <u>www.combanketh.com</u>*

እነዚህን ባንኮች ተጠቅሞ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚቀጥሉት
የሂሳብ ቁጥር መላክ ይችላል

**A. Dollar Account**

**The Commercial Bank of Ethiopia, Churchill Avenue**
**Trade Service**
**Foreign transfer NR/NT Accounts**
**Account No. 2070255950700**
**SWIFT Code CBETETAA**

**B. Euro Account**

**The Commercial Bank of Ethiopia, Churchill Avenue**
**Trade Service**
**Account Name: ----- Millennium Dam Bond**
**Account No: ----- 0270255774200**
**Branch Name: ---- Foreign Transfer & NR/NT Accounts**
**SWIFT Code: ---- CBETETAA, Addis Ababa, Ethiopia**

***ቦንዱን በመግዛት በታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ግንባታ አሻራዎን ያኑሩ!***